Letter to Parents from the Chancellor (Amharic)

DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

ሰኔ (June) 29, 2016

ውድ የዲሲፒኤስ ወላጆች እና የማኅበረሰብ አባላት፣

በጥቅምት (October) 1, 2016፣ የዲሲፒኤስ ቻንስለርነቴን ተግባር አገባድዳለሁ። ይህንንም በቀላሉ ለመግለጽ፣ አዲስ የሕይወት ጉዞ ለመጀመር ዝግጁ ሆኜ የምገኝ እና በዲሲፒኤስ የገነባነው ቡድን ሥራችንን ወደፊት በአዲስ አመራር ሥር ለማራመድ ዝግጁ ለመሆኑ ሙሉ እምነት አለኝ።

የአለፉት ዘጠኝ ዓመታት ዕውነተኛ ቱርፋቶች ነበሩ። በዲሲፒኤስ፣ መጀመሪያ እንደምክትል እና በኋላም ሙሉ ቻንስለር ሆኜ ማገልገል ስጀምር፣ መላ ቀሪ ሕይወቴን በሙሉ በደስታ የሚያበረታታ እድሎች ነበሩኝ። ልክ ለተማሪዎቻችን እንደሆነው፣ ለእኔ በጉልህ ተቀምጠው የሚታዩኝ ግሩም የስታቲስቲካዊ ስኬቶች ወይንም እያደጉ በመሄድ ላይ ያሉ የተማሪዎቻችን የፈተና ውጤቶች አይደሉም። ከሁሉም በላይ ለእኔ ይገቹው ያለሁት ውድ የደስታ ትውስቶቼ በዲሲፒኤስ በቆየሁባቸው ዘመናት ያገኘኋቸው ሰዎች እና ገጠመኞቼ ናቸው።

በአለፉት ዘጠኝ ዓመታት በኦቲዝም (autism ማለትም የግኑኝነቶች እና የመግባባት ማኅበራዊ ችግሮች ያሏቸው) ተማሪዎችን በበሮውስ (Burroughs ES) አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመሳሰሉ በተግባር ላይ የተመለከትኳቸውን ክፍሎች ወይንም እንደገና በተገነባ በባሉ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ምድረ ግቢ (Ballou HS campus) በተገኘሁበት ጊዜ በዚያ የሚያስተምሩ ግሩም የትምህርት ባለሙያዎች ማየቴን አስታውሳለሁ።

በየዕለቱ ለተማሪዎቻችን ታላቅ ትምህርት ቤቶችን ለመፍጠር ራሳቸውን ለሥራ መስዋዕት ያደረጉ እና ከልብ በታታሪነት የሚሠሩ የእያንዳንዱን የተማሪዎቻቸውን ስም የሚያውቁ እና የእያንዳንዱንም ተማሪ የመማር ፍላጎት ለማርካት በታታሪነት የሚሠሩ ግሩም ርእሳነ መምህራኖቻችችንን አስታውሳለሁ።

አብሬአቸው በመሥራት ከፍተኛ ስሜት ያሳደሩብኝ እና ለልጆቻቸው ፍቅር እና ቆራጥነት፣ አቋም ያላቸውን ወላጆች አስታውሳለሁ። ምንም እንኳን በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ዘወትር ስምምነት የነበረን ባይሆንም፣ ለተማሪዎቻችሁ በጽኑነት እና በቁርጠኝነት መቆማችሁን ዘወትር ምን ጊዜም ግምት እና አድናቆት የምሰጠው ነው።

ምናልባት ከሁሉም ነገር በላይ እጅግ ጎልቶ የሚታየው፣ ተማሪዎቻችን፣ ትምህርት እየቀሰሙ እና እያደጉ፣ እየጎለበቱ በመጓዝ ትውስቴ ሆኖ የሚቆየው በእያንዳንዳቸው የሚንጸባረቀው ብርሃን ነው። ተማሪዎች፣ የውጪ ሀገራትን ሲጎበኙ፣ ለማንበብ ሲማሩ፣ ብስክሌት ለመጋለብ ሲጥሩ፣ እና ከፕሪዜዳንቱ እና ከተቀዳሚዋ እመቤት ጋር ሲገናኙ ተመክቻለሁ። በእነዚህ በእያንዳንዳቸው ገጠመኞች እና በሌሎችም በመቶዎች በሚቆጠሩ ልምዶች ምክንያት የተማሪዎቻችን ዓላማት እያድጉ እና እየሰፉ ሲጓዙ ተመልክቻለሁ።

ወደ አዲስ ተፈታታኝ ሁኔታዎች እና ገጠመኞች ስጓዝ፣ ከማንኛቸውም ጉዳይ በላይ ሁሉ ቀረብኝ፣ አመለጠኝ የምለው ይኸው ነው።

በአለፉት ዘጠኝ ዓመታት፣ ዲሲፒኤስ፣ ከአዲስ ቻንስለሮች እስከ አዲስ ከንቲባዎች፣ አዲስ ርእሠ መምህራን ድረስ በበርካታ ሽግግራዊ ለውጦች ውስጥ ተጉዟል። በእነዚህም ሽግግራዊ የለውጥ ሂደቶች አማካይነት ዲስሪክቱ አድጓል። በጥቅምት (October) 1, 2016፣ በእኔ ስንብት ዲስትሪክቱ በአዲስ መሪ አማካይነት የማበብ እና የመጎልበት እድል ያገኛል።

የትምህርት ቤቶች ዲስትሪክታችንን፣ አመራር ለመቀጠል ስለሰጡኝ እድል እና በዚህም ሽግግሬ ወቅት ስላደረጉልኝ ድጋፍ ለከንቲባ ባውዘር (Mayor Bowser) ከፍ ያለ ምሥጋና አቀርባለሁ። ከንቲባ ባውዘር፣ ከበርካታ ግሩም የዲሲፒኤስ ቡድን አባላት መካከል፣ ጆን ዴቪስ (John Davis) ከጥቅምት (October) 1 ጀምሮ ጊዜያዊ የሽግግር የትምህርት ቤቶች ኃላፊ ሆነው እንዲያገለግሉ ስለመረጧቸው በጣም ተደስቻለሁ። 1. ጆን (John) በትምህርት መስከ ከሁለት ዐሥርተ ዓመታት በላይ መምህር፣ ርእሠ መምህር እና እንደ የዲስትሪክት መሪ ሆነው አገልግለዋል። እሳቸው በተጨማሪ የዲሲፒኤስ ተማሪ ወላጅ ሲሆኑ ተማሪዎቻችንን ሁሉ ለማገልገል ጠንካራ አቋም አላቸው። በ ጆንስ (John) አመራር ሥር፣ ርእሠ መምህራንን፣ እና የማዕከላዊው ጽሕፈት ቤት ሠራተኞቻችንን ጨምሮ በርካታ የቡድን አባሎቻችችን ሥራቸውን እንዲቀጥሉበት ተስፋ አደርጋለሁ።

አብረን አንድ ላይ ባከናወናቸው ተግባራት ኩራት የሚሰማኝ ሲሆን ዲስትሪክታችን መጎልበቱን እና ፍሬያማ መሆኑን እየቀጠለበት እንደሚጓዝ ለማየት በጉጉት እጠባበቃለሁ።

ከልባዊ አክብሮት ጋር፣

Kaya Henderson
ቻንስለ (Chancellor)